በንግድና ቀጠናዊ ትሥሥር ሚኒስቴር የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን

# የነዳጅ ማደያ በሌለባቸው ከተሞች እና አካባቢዎች የነዳጅ የችርቻሮ ንግድ ፈቃድ አሰጣጥና የቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 906/2014

አዲስ አበባ

2014 ዓ.ም

የፌዴራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19(4) መሰረት የንግድና ቀጠናዊ ትሥሥር ሚኒስቴር ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የነዳጅ ማደያ በሌለባቸው ከተሞች እና አከባቢዎች የነዳጅ የችርቻሮ ፈቃድ አሰጣጥና የቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 906/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2 ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1/ "የነዳጅ ውጤት" ማለት ከተፈጥሮ ድፍድፍ ነዳጅ እና ከፔትሮሊየም ጋዝ፣ ባዮ-ፊውል ወይም ሴንቴቲክ ነዳጅን ከማጣራት ወይም ከማቀናበር የተገኘ ንፁህ ወይም አግባብ ባለው መንገድ የተደባለቀ የነዳጅ ውጤት ሆኖ ቤንዚንን፤ ኬሮሲንን፣ ናፍጣን፣ ቀላልና ከባድ ጥቁር ናፍጣንና የአውሮፕላን ነዳጅን ያካትታል፣

2/ "የግብይት ተሣታፊ" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን የሚያስመጣ፣ የሚያጣራ፣የሚያደባልቅ፣ የሚያከማች፣ የሚያከፋፍል፣ የሚቸረችር፣ የሚያጓጉዝ፣ የሚልክ እና መሰል ተግባራትን እንዲያከናውን ፈቃድ የተሰጠው ሰው፣

3/ "የብቃት ማረጋገጫ" ማለት የነዳጅ ውጤቶች መያዣ፣ማከማቻ፣ማጓጓዣ እና የችርቻሮ መሸጫ መስፈሪያና የደህንነት መጠበቂያ ብቃትን በማረጋገጥ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፡፡

4/ "ባለሥልጣን" ማለት የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ነው፡፡

5/ "ባለድርሻ አካላት" ማለት የክልል እና የከተማ አስተዳደር እና በተዋረድ ያሉ ንግድን የሚመሩ አካላትና የነዳጅ ማደያዎች ናቸው፡፡

6/ "የነዳጅ አዳይ" ማለት ነዳጅን ከነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያ ገዝቶ ለተጠቃሚውና ነዳጅ ማደያ በሌለባቸው ከተማና አካባቢዎች ለሚቸረችር ሰው የሚሸጥ ነው፡፡

7/ "የነዳጅ ቸርቻሪ ነጋዴ" ማለት መደበኛ የነዳጅ ማደያ መሠረተ ልማት በሌለባቸው ከተሞችና አካባቢዎች የነዳጅ ውጤቶችን እያቀረበ በችርቻሮ እንዲሸጥ የተፈቀደለት ድርጅት ወይም ሰው ነው፤

## አንቀጽ 3 የመመሪያው አስፈላጊነት

የነዳጅ ማደያ በሌለባቸው ከተሞች የሚደረገው የነዳጅ ችርቻሮ ንግድ የሚመራበት፣ የነዳጅ ዋጋ የሚወሰንበት፣ ቁጥጥር የሚደረግበትና የአካባቢ ደህንነት የሚጠበቅበት የአሠራር ሥርዓት ባለመኖሩ ለተጠቃሚው የሚቀርበው ነዳጅ ተገቢ ባልሆነ ዋጋ እና በህገወጥ ንግድ መልክ የሚሰራ በመሆኑ ይህንኑ የአሠራር ክፍተት ለመሙላት ታስቦ የተዘጋጀ መመሪያ ነው፡፡

## አንቀጽ 4 የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በነዳጅ ማደያ እና ከነዳጅ ማደያ በታች በነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድ ላይ በሚሳተፉና ይህንን ተግባር በሚያስፈጽሙ ተቆጣጣሪ አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 5 አግባብነት ያላቸው ተቆጣጣሪ አካላት ተግባር

1/ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ግባራት ያከናውናል፡-

- ሀ) የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ ንግድ ሕጋዊ ሥርዓቱን ተከትሎ መከናወኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
- ለ) የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድን የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት እንዲከታተሉት ያስተባብራል፣በሥራ ሂደት ላጋጠሙ ችግሮች መፍትሄ ይሰጣል፣
- ሐ) ማደያ በሌለባቸው ከተሞች እና አካባቢዎች የሚደረገውን የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ቀመር አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል ሲወሰን ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤
- መ) የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድ ላይ የሚሳተፉ ተቋማትን የትርፍ ሕዳግ ቀመር ማሻሻል ሲያስፈልግ አዘጋጅቶ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲወሰን ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣
- ሠ) መመሪያውን ያላከበሩ ወይም የጣሱ የነዳጅ ውጤቶች ቸርቻሪዎች ላይ አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣

2/ የነዳጅ ችርቻሮ ዋጋ አተማመን

- ሀ) ነዳጅ ማደያ በሌለባቸው የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ሲተመን መሠረት የሚደረገው የማደያ መሸጫ ዋጋ፣ የትራንስፖርት (አስፋልት/ጠጠር)፣ የመጫኛና የማራገፊያ ወጪ፣ ብክነትና ትነት፣ የቸርቻሪው የትርፍ ህዳግን ያካትታል፣

ለ) ማደያ በሌለባቸው ከተሞች የነዳጅ የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በሚከተለው ቀመር መሰረት ይሰላል፣

1. ከነዳጅ ማደያ መግዣ ዋጋ (ሀ)
2. የትራንስፖርት ወጪ (ለ)
    - በአስፋልት መንገድ -------------- ብር 0.008/ኪ/ሜ/ሊትር
    - በጠጠር መንገድ ------------------ ብር 0.01/ኪ/ሜ/ሊትር
3. የማስጫኛና ማውረጃ ወጪ (ሐ) --------- ብር 0.10/ሊትር
4. የብክነትና ትነት ወጪ (መ) ---------------- ብር 0.02/ሊትር
5. የቸርቻሪ የትርፍ ህዳግ --------------------- [(ሀ)+(ለ)+(ሐ)+(መ)]*5 በመቶ

## 3/ የክልልና የከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮዎች ተግባር፣

ሀ) ነዳጅ ማደያ በሌለባቸው ከተሞች እና አካባቢዎች የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድ የተፈቀደላቸው ድርጅቶች እና ግለሰቦች በአካባቢው ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች በትክክል ስለመሸጣቸው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ ያደርጋሉ፣

ለ) የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ተመን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚወስነው ቀመር መሠረት በትክክል መሠራቱን የክትትልና የቁጥጥር ተግባራትን ያከናውናሉ፣

ሐ) የነዳጅ ቸርቻሪ ነጋዴ ለተጠቃሚዎች የሚያቀርበውን የነዳጅ ውጤቶች ከሌሎች ባዕድ ነገሮች ጋር ቀላቅሎ እንዳይሸጥ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ ያደርጋሉ፣

መ) የነዳጅ ውጤቶችን የችርቻሮ ንግድ አፈጻጸም መረጃዎችን በማደራጀት በየወሩ ለባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ሪፖርት ያደርጋሉ፣

ሠ) የነዳጅ ማደያ መሰረተ ልማት እንዲስፋፉ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

## 4/ በዞን ንግድ መምሪያዎች የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድን ለመቆጣጠር የሚከናወኑ ተግባራት፣

ሀ) የነዳጅ ቸርቻሪ ነጋዴ የገዛውን የነዳጅ ውጤቶች ጥራቱንና ደህንነቱን ጠብቆ በተተመነው ዋጋ ለአካባቢው ህብረተሰብ መሸጡን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣

ለ) የነዳጅ ማደያ የሌለባቸውን ከተሞችና አካባቢዎችን በመለየት ለክልልና ለባሥልጣን መ/ቤቱ ያሳውቃል፣

ሐ) የነዳጅ ችርቻሮ ፈቃድ ለማግኘት የነዳጅ ማደያ ካለበት ቢያንስ 20 ኪሎ ሜትር መራቁን መረጋገጫ ይቀርባል፣

መ) ማደያ የሌለባቸው ከተሞችንና አካባቢዎች ቅርብ ከሆኑ ማደያዎች ጋር ያስተሳስራል፣

ሠ) ከየወረደው የሚቀርብለትን የነዳጅ ፍላጎት መሠረት በማድረግ ማደያ በሌለባቸው ከተሞችና አካባቢዎች ነዳጅ በችርቻሮ እንዲቀርብ የአቅርቦት መጠንን መሠረት ያደረገ የነዳጅ ቸርቻሪ ብዛት ይወስናል፣

ረ) ነዳጅ ቸርቻሪው ለተፈቀደለት ከተማና አካባቢ ፍጆታ ብቻ የሚውል ነዳጅ ከማደያው እንዲሸጥለት ትሥሥር ይፈጥራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

ሰ) ነዳጅ ማደያ በሌለባቸው ቦታዎች የነዳጅ ማደያ መገንባት ለሚፈልጉ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የግንባታ ቦታ እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፣

ሸ) የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ ግብይት አፈጻጸም ሪፖርት ከነዳጅ ከማደያ፣ ከቸርቻሪውና ከወረዳው መረጃ በመሰብሰብና በማደራጀት ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ቅጽ 9 መሠረት በየወሩ ለክልል መንግስት ሪፖርት ያቀርባል፣

ቀ) የነዳጅ ውጤቶችን በችርቻሮ እንዲያቀርቡ ለተፈቀደላቸው ቸርቻሪዎች ወርሀዊ የነዳጅ ፍላጎት ዓይነትና መጠን በመጥቀስ እንዲሸጥላቸው ትሥሥር ለተደረገላቸው የነዳጅ ማደያዎች ያሳውቃሉ፡፡

በ) ለነዳጅ ውጤቶች ቸርቻሪ ነጋዴ ስለነዳጅ አያያዝና ደህንነት በተመለከተ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት አለበት፡፡

## 5/ በወረዳ ንግድ ጽ/ቤቶች የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድን ለመቆጣጠር የሚከናወኑ ተግባራት፣

ሀ) በወረዳው የሚገኙትን የነዳጅ ውጤቶች የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች፣ ኢንዱስትሪዎች (ወፍጮ) ጀኔሬተሮችና ሌሎች የነዳጅ ውጤቶችን ፍላጎት ዓይነትና መጠን በማጥናት ለዞኑ ያቀርባሉ፣

ለ) የነዳጅ ችርቻሮ ፈቃድ ለሚጠይቁ ቸርቻሪ ነጋዴዎች ለወረዳው ከሚያስፈልገው የነዳጅ መጠን ውስጥ ለአካባቢው መቅረብ የሚገባውን የነዳጅ መጠን በመወሰን የድጋፍ ደብዳቤ ለዞኑ ይጽፋሉ፣

ሐ) የነዳጅ ቸርቻሪው ነጋዴ ከተፈቀደለት የነዳጅ ማደያ የገዛውን የነዳጅ ውጤቶች ለተፈቀደለት ከተማ እና አካባቢ ብቻ ማቅረቡንና ለተጠቀሚው ህብረተሰብ መሸጡን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

መ) ከነዳጅ ማደያ እና ከነዳጅ ቸርቻሪው ነጋዴ በወር ውስጥ የተገዛውንና የተሸጠውን ነዳጅ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ ቅጽ 9 መሠረት መረጃ በመሰብሰብ ያደራጃል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በየወሩ ለዞን ሪፖርት ያቀርባል፣

ሠ) የነዳጅ ማደያ በሌለባቸው ከተሞችና አካባቢዎች ማደያ መገንባት ለሚፈልጉ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የግንባታ ቦታ እና ኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፣

ረ) ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት መሰረት መስፈርቱ መሟላቱን በማረጋገጥ የብቃት መረጋገጫ ይሰጣል፣

ሰ) ተቆጣጣሪው አካል የሚሰማራበት የቁጥጥር ዕቅድና መረሐግብር ያለው ሆኖ ነገር ግን እንደ አስፈላጊነቱ  በድንገት ሊከናወን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 6 ነዳጅ ማደያ በሌለባቸው ከተማዎችና አካባቢዎች ለነዳጅ ችርቻሮ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች፣

1/ ፈቃድ ጠያቂው እንዲፈቀድለት የሚፈልገውን የነዳጅ ዓይነትና መጠን የሚገልጽ ከወረዳ ወይም ከከተማ መስተዳድር ንግድ ጽ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ ለዞን ማቅረብ አለበት፣

2/ የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድ የሚካሄድበት ቦታ ከመኖሪያ ቤትና ከሌሎች ከንግድ ቤቶች የተለየ የአካባቢን ደህንነት ጠብቆ የሚሠራበት ቦታ ስለ መሆኑ እና የመያዣ፣ የማከማቻ፣ እና የመሥፈሪያ ዕቃዎች የብቃት መረጋገጫ ሰነድ ከወረዳ ወይም ከከተማ መስተዳድር ንግድ ጽ/ቤት መቅረብ አለበት፣

3/ የነዳጅ ማከማቻውን የመያዝ አቅም የሚያረጋግጥ ሰነድ ከንግድ ጽ/ቤት ማቅረብ አለበት፤

4/ አዲስ ወይም የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ 7 የነዳጅ ማደያ በሌለባቸው ከተሞችና አካባቢዎች የነዳጅ ቸርቻሪ ግዴታ

1/ ከነዳጅ ማደያ የገዛውን የነዳጅ ውጤቶች በዚህ መመሪያ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች ላይ የተቀመጡ ግዴታዎችና ክልከላዎችን አክብሮ መሥራት አለበት፤

2/ የተፈቀደለትን የነዳጅ ውጤቶች ለተፈቀደለት ከተማ/አካባቢ ብቻ ጥራቱን በጠበቀ መልኩ በትክክለኛ መስፈሪያ እና በተተመነው ዋጋ ብቻ መሸጥ አለበት፤

3/ የገዛውንና የሸጠውን የነዳጅ መጠን እና ዓይነት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ ቅጽ 10 መሠረት መረጃ አደራጅቶ መያዝ፣ በየቀኑ ለወረዳው ንግድ ጽ/ቤት ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

4/ በሚመለከተው አካል ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ ለተፈቀደላቸው አካላት መተባበር አለበት፤

5/ የነዳጅ ውጤቶች እንዲያቀርብለት ከተዋዋለው የነዳጅ ማደያ ውጭ ከሌላ ማደያ መግዛትና ከተፈቀደለት የመሸጫ ቦታ ውጭ መሸጥ የተከለከለ ነው፤

6/ የነዳጅ ችርቻሮ መሸጫ ቦታ ላይ በግልፅ የሚታይ የመሸጫ ዋጋና ታፔላ መለጠፍ አለበት፡፡

## አንቀጽ 8 የነዳጅ አዳይ ግዴታ

1/ ፈቃድ ለተሰጠውና ትሥሥር ለተፈጠረለት ቸርቻሪ በገባው ውል መሠረት የነዳጅ ውጤቶችን ማቅረብ አለበት፤

2/ ነዳጅ አዳዩ ለነዳጅ ቸርቻሪው ነጋዴ የሸጠውን የነዳጅ መጠን እና ዓይነት መረጃ በመያዝ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘ አባሪ ቅጽ 8 መሠረት በየወሩ ለወረዳና ለዞን ንግድ ቢሮዎች ሪፖርት ማቅረብ አለበት፤

3/ ከተፈቀደለት እና ውል ከፈፀመው የነዳጅ ውጤቶች ቸርቻሪ ነጋዴ ውጭ ላልተፈቀደለት ሌላ ቸርቻሪ መሸጥ የለበትም፤

## አንቀጽ 9 የነዳጅ ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ኃላፊነት

1/ የነዳጅ ውጤቶች የችርቻሮ ግብይትን በተመለከተ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰነዶቹን ፎቶ ኮፒ በማድረግ፣ ፎቶ ግራፍ በማንሳት መረጃዎችን በማሰባሰብ ለሚመለከተው አካል ማሳውቅ አለበት፤

2/ ቁጥጥር በሚያደርግበት ወቅት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከሚመለከተው የአከባቢው ፖሊስ እና የፍትህ አካላት ድጋፍ መጠየቅ ይችላል፣

3/ ተቆጣጠሪ ባለሙያዎች ተቆጣጣሪ ስለ መሆናቸው የሚገልፅ የመስሪያ ቤት መታወቂያ ወረቀት እና የሥራ ትእዛዝ ደብዳቤ መያዝና ቁጥጥር ለሚደረግበት ድርጅት ማሳየት አለባቸው፤

4/ በቁጥጥር ሥራ ወቅት የታየውን ጉድለት ለድርጅቱ ባለቤት ወይም ህጋዊ ተወካይ የማሳወቅ እና በቁጥጥር ወቅት በታዩ ግኝቶች ላይ በቼክ ሊስቱ መሠረት መፈራረም አለባቸው፤

5/ ተቆጣጣሪው አካል ለቁጥጥር ሲወጣ የቁጥጥር ተግባራትን ለማስተባበር የተመደበው አግባብ ያለው ኃላፊ ጋር ስለሚቆጣጠረው ቸርቻሪ እና ስለሚደረገው ቁጥጥር ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ቅጽ 10 መሠረት ስምምነት ያደርጋሉ፤

6/ ተቆጣጣሪው አካል ባደረገው ቁጥጥር ያገኘውን ውጤት በዚህ መመሪያ አባሪ ቅጽ 10 በመሙላት ቁጥጥር ከተደረገበት ቸርቻሪ ጋር በመፈራረም ለቁጥጥር አስተባባሪው ያቀርባል፤

7/ ተቆጣጣሪው አካል የቁጥጥር ተግባሩ አስገዳጅ በሆነ ምክንያት ከመንግሥት የሥራ ስዓት ውጪ የሚያከናውን ከሆነ አግባብ ካለው ባለሥልጣን የትእዛዝ ደብዳቤ በመያዝና ቁጥጥር ለሚደረግበት ድርጅት ማሳየት አለበት፡፡

## አንቀጽ 10 አስተዳደራዊ ቅጣት

1/ የነዳጅ ቸርቻሪ

ሀ) ማንኛውም የነዳጅ ማደያ በሌለባቸው ከተሞችና አካባቢዎች የነዳጅ ውጤቶች ቸርቻሪ የሆነ አካል የገዛውንና የሸጠውን የነዳጅ መረጃ በማደራጀት በየሳምንቱ ለወረዳ ንግድ ጽ/ቤት ሪፖርት ካላደረገ ወይም ለተቆጣጣሪዎች የሚጠይቁትን መረጃ ለመስጠት ካልተባበረ የፅሁፍ ማስጠንቀቅያ ይሰጠዋል፤

ለ) ማንኛውም ነዳጅ ማደያ በሌለባቸው ከተሞችና አካባቢዎች የነዳጅ ውጤቶች ቸርቻሪ የሆነ አካል የፅሁፍ ማስጠንቀቅያ ተሰጥቶት ድጋሚ ተመሳሳይ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ፣ መያዝ ያለበትን ሰነዶች ያልያዘ እንደሆነ፣ የሚሠራበት ቦታ ላይ የነዳጅ መሸጫ ዋጋ እና ታፔላ ያልለጠፈ ከሆነ፣ ከተፈቀደለት የመሸጫ ዋጋ በላይ የሸጠ እንደሆነ፣ ከተፈቀደለት የመሸጫ ቦታ ውጪ የሸጠ እንደሆነ፣ ጥራት የሌለው የነዳጅ ውጤቶች ሲሸጥ የተገኘ እንደሆነ እና ትክክለኛ ባልሆነ መሥፈሪያ ተጠቅሞ ሲሸጥ የተገኘ እንደሆነ የጥፋቱ ክብደትና ያደረሰውን ጉዳት በማየት የተሰጠው ፈቃድ ይታገዳል፣ ይሠረዛል፡፡

2/ ተቆጣጣሪ አካል

በየእርከኑ የቁጥጥር ሥራ እንዲሠራ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም አካል በአዋጅ ከተሰጠው ሥልጣንና በዚህ መመሪያ ላይ ከተዘረዘረው አሠራር ውጭ የቁጥጥር ሥራ ሲያከናውን የተገኘ አካል እንደየጥፋቱ ክብደት በዲሲፒሊን ስነ-ስርዓት ከመጠየቅ እስከ ከሥራ ማሰናበት የሚያደርስ እርምጃ እንዲወሰድበት ይደረጋል፡፡

3/ በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጠ አስተዳደራዊ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀልና በፍትሐ-ብሔር ውይም ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

4/ የነዳጅ አዳይ

ሀ) ማንኛውም የነዳጅ አዳይ የሥራ አፈፃፀሙን በተመለከተ በየወሩ ለወረዳና ለዞን ሪፖርት የማያደርግ ከሆነ ወይም ለቁጥጥር የሚላኩ ተቆጣጣሪዎች የሚጠይቁትን መረጃ ለመስጠት የማይተባበር ከሆነ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

ለ) ማንኛውም የነዳጅ ውጤቶች አዳይ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በድጋሚ ተመሳሳይ ድርጊት ሲፈፅም የተገኘ እንደሆነ፣ የነዳጅ ውጤቶች በድርጅቱ ውስጥ እያለ የለም በማለት የቸርቻሪ ነጋዴዎችን ስራ ያስተጓጎለ እንደሆነ፣ ጥራት የሌለው የነዳጅ ውጤቶች ሲሸጥ የተገኘ እንደሆነ፣ በመንግሥት ከተተመነው የመሸጫ ዋጋ በላይ ሲሸጥ የተገኘ እንደሆነ እንደጥፋቱ ክብደትና ያደረሰው ጉዳት መሰረት የተሰጠው ፈቃድ ይታገዳል /ይሠረዛል፡፡

ሐ) በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጠ አስተዳደራዊ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀልና በፍትሐ-ብሔር ውይም ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 11 የመተባበር ግዴታ**

ተቆጣጣሪው አካል ይህን መመሪያ በማስፈፀም ሂደት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአካባቢው ፖሊስ እና የፍትህ አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 12 ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ህጎች**

በዚህ መመሪያ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተቀመጡ ሆኖ የነዳጅና ኢነርጂ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ፣ የወንጀል፣ የፍትሐብሔር ህጎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 13 መመሪያውን ስለ ማሻሻል**

የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን መመሪያው መሻሻል ይገባዋል ብሎ ሲያምን በማንኛውም ጊዜ የማሻሻያ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ በማቅረብ እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 14 መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ከሰኔ 8 ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አቶ ገብረመስቀል ጫላ**

**የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር**

**አዲስ አበባ**